# የወያኔ አገዛዝ ዕድሜ ቀጣዮች

የመለስ ዜናዊ መንግሥት አገዛዙን ለማራዘም የሚተማመነው በጠመንጃ ኃይል መጠቀም፣ በሞኖፖል በያዛቸው ዜና ማሰራጫዎች ሕዝቡን ማወናበድ፣ አገሪቱ በብድርም በምጽዋትም የምታገኘውን ገንዘብ ከሕዝብ አፍ እየነጠቀ በውጭ አገር ሎቢስቶችን በመግዛትና በየከተማው አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ የሚባሉ የብርሃኑ ነጋ መልዕክተኞች በቅንጅት ሥም ያደራጃቸውን ቡድኖች እንዲያወናብዱ በማድረግ ነው።

አገር ቤት ሆነው አገዛዙን የሚቃወሙትን ወገኖች የመለስ የጸጥታ ኃይሎች ያስፈራራሉ፣ያስራሉ፣ ይገድላሉ። ለዚህ ሥራ መለስ ያደራጀው ሕጻናት ሳይቀሩ የጨፈጨፍ ደም የተጠማው ነፍሰ ገዳይ የአግዐዚ ጦር በወገኖቻችን ላይ ያደረሰውን ዕልቂት አይተናል።

የመለስ አገዛዝ ሥርዐት ፍርድ ቤቶች ፍትህ የሚገኝባቸው ተቋሞች ሳይሆኑ የአገዛዙን ትዕዛዝ በመፈፀም ተቃዋሚዎች ላይ በሕግ ሽፋን የግፍ እሥራትን የሚፈርዱ የሕግ ቲያትር የሚታይባቸው መድረኮች ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለአገሩ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታ ወቅታዊ መረጃዎችን አያገኝም። በውጭ አገር የሚሠራጩ ዜናዎች እንዳይደርሱት የኢንተርኔትና የሬዲዮ ሥርጭቶችን እነ መለስ አግደዋል። በምትኩ የራሳቸውን “ፍትሐዊ” አስተፈዳደር ጥሩነትና ያስገኘውን “ዕድገት” በሚሰብኩ የዜና ማሰራጫዎች ሕዝቡን ያደነቁሩታል።

ፍትህ መጥፋቱን፣ ሰብዐዊ መብት መረገጡን፣ የአስተዳደር ብልሹነት መስፈኑን ለማስተባበልና የውጭ ደጋፊዎቹን ለማስደሰት የመለስ መንግሥት ለባዕዳን ኃይሎች ተላላኪነቱንና ሽር ጉድ ባይነቱን በተግባር አስመስክሯል። ይህም ሽር ጉድ ባይነቱ የዲፕሎማሲና፡ የመሣሪያ ዕርዳታ ስለሚያስገኝለት የአገዛዝ ዕድሜውን ትንሽ ያራዝምለት ይሆናል።

በአገር ውስጥ የሚገኙ ተቃዋሚዎችን የሚያፍነውን ያህል በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎችን ዝም ለማሰኘት ችሎታው ስለሌለው መለስ የፈጠረው ዘዴ በቅንጅት ሥም ተለጣፊ ቡድኖችን ማቋቋምና ማጠናከር ነው። ስለሆነም አንዳርጋቸው ጽጌና ብርሃነ መዋ የሚባሉ የብርሃኑ ነጋ ጭቃ ሹሞች በቅንጅት ድጋፍ ሥም በየከተማው ያሰባሰቧቸውን ቡድኖችን በማጠናከር ላይ ይገኛል።

በጦር ኃይል ጭምር የሚታገል “ግንቦት 7” የተሰኘ ፓርቲ መሥርቻለሁ ሲለን ቅንጅት በግርግር ውስጥ የነበረ ጊዜ አጋጣሚውን ተጠቅሞ አሥርጎ በጓሮ በር ያስገባትና ከቅንጅት የተባረረችው ወይዘሮ ብርቱካን ደግሞ የራሷን “አንድነት ለደሞክራሲና ለፍትህ” የሚባል አንጃ ፓርቲ ፈጥራለች። የፖለቲካ ፓርቲዎች ዕጥረት ያለብን ይመስል። እነ እንዳርጋቸው ያቋቋሟቸው ተለጣፊዎች የማንን ድርጅት እንደሚከተሉ ግራ ተጋብተው ነበር። “ካፈርኩ አይመልሰኝ” ብለው ሁለቱንም አንጃዎች እንደግፋለን እያሉ ሲንገታገቱ ይታያሉ። የመለስ ወኪሎች አንጃዎቹን የሚደግፉትን ስብስቦች መጠናከር ይፈልጋሉ። ለምን? ካሁን በፊት በየከተማው የሚኖረውን የኢትዮጵያውያን ኮሚኒቲ በሚያሳዝን ሁኔታ በማወናበድ የቅንጅትን የውጭ ድጋፍ ለማዳከም በመቻላቸው ወደፊትም እነዚህ ቡድኖች ተመሳሳይ ሳቦታጅ ለማድረግ ስለሚችሉና ለአገዛዙ ዕድሜ ስለሚጨምሩ የነመለስ ሰላዮች ይፋ ባልሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ

በቡድኖቹ እጅ በሚገባ ከፍተኛ ወጪ እያጠናከሯቸው ይገኛሉ፡፡ በውጭ አገር ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ቅንጅት ሊያገኝ የሚችለውን የገንዘብ፣ የሞራልና የዲፕሎማሲ ድጋፍ እንዲያጣ የሚደረገው ጥረት በአንጃዎቹ መሣሪያነት ቀጥሏል፡፡

ተለጣፊዎቹ ቡድኖች ሕዝባዊነታቸውን እንዲያሳይላቸው ብለው የ1997 ሕዝባዊ ምርጫና ወይዘሮ ብርቱካን ሚዴቅሳን ሊያገናኙ ይሞክራሉ፡፡ በምርጫ 97 ወቅት ወይዘሮዋ ወልዳ እመጫት እንደነበረች፣ ለቅንጅት ምርጭ መወዳደር ቀርቶ በየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ አባል እንዳልነበረች፣ ይልቁንም ቅንጅትን የተቀላቀለችው በመስከረም 1998 ዓ ም እንደነበር ደብቀውን ወይዘሮዋና ተባባሪዎቿ የመሠረቱት አንጃ ሲያደንቁና ሲያወድሱ የአየር ሞገዱችን አጨናንቀዋል፡፡

የወይዘሮ ብርቱካንን የኋላ ታሪክ ለምናውቅ ግን የተሰማን ነገር አድናቂዎቿን ከተሰማቸው የተለየ ነው፡፡ ይልቁንም የበለጠ ጎልቶ የሚታየን ወይዘሮዋና መሰሎቿ ያቋቋሙት አንጃ ለወያኔ የግፍ አገዛዝ መራዘም ዓይነተኛ ተፈላጊ መሣሪያ ሆኖ ለወያኔ በወቅቱ መገኘቱ ነው፡፡ በሕዝብ መስዋዕትነት ላይ የተመሠረተ አንድነትን አፍርሶ የሚገነባ ሌላ “አንድነት” የአስመሳዮችና የአድር ባዮች አካሄድ ነውና፡፡

ሁለቱ የታወቁ የሥልጣን ጥመኞች (ብርሀኑ ነጋና ብርቱካን ሚዴቅሳ) የየራሳቸውን አንጃ መሥርተው ትንሽም ብትሆን “ባለሥልጣን” በመሆናቸው ሕዝብ ለተያያዘው የነጻነት ትግል የሚደርጉትን “አስተዋጽዖ” ለማየት ብዙም አልጓጓንም፡፡ የሁለቱንም ያለፈ ታሪክ ስለምናውቅ፡፡ ተስፋ የምናደርገውና ለማየት የምንጓጓው በሕዝብ ልቦና ውስጥ የሠረጸው እንዲሁም ለራዕዩ መሳካት ሕዝብ የሕይወት መስዋዕትነት የከፈለለት ዕውነተኛው ቅንጅት በብርሀኑ ነጋ መሠሪነት በውስጡ የተንሰራፈጠው ጉፋያ ጸድቶና ተለቃልቆ ወጥቶለት ተሞዳሟጅነት የሌለበት በኢትዮጵያዊ ቅንንነትና አገር ወዳድነት ላይ የተመሠረተ በአዲስ መንፈስና በአዲስ አመራር መጠናከሩ ከልብ ደስ ብሎናል፡፡ ብሩህ ተስፋም ሰጥቶናል፡፡ አዲስ ጅምር ይዘናል፡፡ አዲስ ራዕይ ታይቶናል፡፡ ትግላችን ፍሬ እንደሚያፈራ አንጠራጠርም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል!!